# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 210 ግንቦት 16 2004 ገጽ 1


አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

*"መለስ ዜናዊ አምባገነን ነው!!! መለስ ዜናዊ አምባገነን ነው!!! ነፃነትን እንፈልጋለን!!! መለስ በሰብዕና ላይ ወንጀል የፈፀመ ነው!!! መለስ ወንጀለኛ ነው!!! ምግብ ያለ ነፃነት ምንም ማለት አይደለም!!! እስክንድር ነጋንና ሌሎችን የፖለቲካ እስረኖች ይለቀቁ!!! ነፃነት እንሻለን!!! ነፃነት እንፈልጋለን!!! መለስ አምባገነን ነው!!! ነፃነት እንፈልጋለን!!! ነፃነት!!! ነፃነት!!! ነፃነት!!! ነፃነት!!!"*

መሰስ ዜናዊ በድንጋጤና በላብ የጠመቀ የጋዜጠኛ አበበ ገላው ንግግር

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## በሰሜን አሜሪካ የመለስ ዜናዊ ተጠሪ የሆነው ግርማ ብሩ በቡድን 8 ስብሰባ ላይ የጌታውን ቆሌ የገፈፈውን ተቃውሞ አስመልክቶ መግለጫ ሰጠ

የወያኔ ዘረኛ አገዛዝ በህዝባችን ጫንቃ ላይ ተደላድሎ ላለፉት 21 አመታት እየፈጸመ ያለው ሰቆቃና ሃብት ምዝበራ እንዲሳካለት በታማኝ ጀሌነት ታላቅ አስተዋጾ እያበረከቱ ናቸው ከሚባሉ ሆዳሞች አንዱ መሆኑ የሚታወቅለት ግርማ ብሩ፤ ፕሬዝዳንት ኦባማ ስለ ምግብ ዋስትና መረሃ ግብር እንዲነጋገር ባለፈው ሳምንት ጠርተውት በነበረው አለም አቀፍ ስብሰባ ላይ አለቃውን አንገት ያስደፋ ተቃውሞ በማጣጣል ለፋና ሬዲዮ መግለጫ መስጠቱን ለማወቅ ተችሎአል።

ግርማ ብሩ ለፋና ሬዲዮ ባለፈው ሰኞ በሰጠው መግለጫ፤ አገራችን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ በመቻሏ በፕሬዝዳንት ኦባማና በውጪ ጉዳይ ሚንስትራቸው ሂላሪ ክልንተን በተደጋጋሚ ተወድሳለች በማለት አሁን ላለበት የተደላደለ ኑሮ ያበቃው አለቃው መለስ ዜናዊን ጨምሮ የተለያዩ የሥርዓቱ ቅጠረኞች የወያኔ ፓርላማ ፊት ቀርበው አገርቷ የገጠማትን የምግብ እህል ችግር ለመቅረፍ በበርካታ ሚሊዮን ዶላር ስንዴና ዜይት ከውጪ ተገዝቶ እንዲከፋፈል ሙከራ ቢደርግም ችግሩን ለመቅረፍ እንዳልተቻለ ከመናገራቸው ጋር የሚጻረር ውሸት ውስጥ ተዘፍቆአል።

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ቅጥረኞች አለቃቸው መለስ ዜናዊ እየዘረፈ በሚያዘርፋቸው የህዝብ ገንዘብ የተደላደለ ኑሮ መመስረት በመቻላቸው ብቻ የእህል ምርት እጥረት በፈጠረው የኑሮ ውድነት ህዝባችን ምን አይነት የቁም ስቅል ህይወት እየገፋ እንዳለና በቀን አንድ ጊዜ እንኳ መመገብ መቻል ቅንጦት ሆኖ ስንቱ እስከነ ቤተሰቡ በረሃብ አለንጋ እየተሰቃየ እንደሆነ ለማወቅ ከማይፈልጉበት ደረጃ ላይ መድረሳቸውን የግርማ ብሩ የሃሰት ምስክርነት ማረጋገጫ ነው።

መለስ ዜናዊ ዋሽንግተን ዲስ በሚገኘው የሬጋን ህንጻ ውስጥ በተደረገ የምግብ ዋስትና መርሃግብር ስብሰባ ላይ የተለመደውን የቅጥፈት ንግግር ሲያደርግ በተቃውሞ ያስቆመው የጋዜጠኛ አበበ ገላው ንግግርና መለስ ዜናዊ መድረክ ላይ ሆኖ በድንጋጤ አንገቱን ሲደፋ የሚያሳይ በኢሳት የቪዲዮ ጋዜጠኛ የተቀረጸ ምስል አገር ውስጥና ከአገር ውጪ በኢንተርኔት አማካይነት በመሰራጨቱ የተደናገጡት የወያኔ ቁንጮዎችና ጀሌዎቻቸው (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የፕሬስ ነጻነትን ጨምሮ የዜጎችን መብት እንዲያከብር የአሜሪካ ባለስልጣናት እየጠየቁ ነው

የቀድሞው የአፍሪካ ጉዳዮች ሊቀመንበርና አሁን ሽብርተኝነትን፣ አውዳሚ የጦር መሳሪያን እና ንግድን የሚመለከቱ ጉዳዮችን የሚመለከተውን ኮሚቴ የሚመሩት ኤድዋርድ ሮይሲ ለአምባገነኑ መለስ ዜናዊ በጻፉት ደብዳቤ፣ በእስር ላይ ስለሚገኙት ጋዜጠኞችና የፖለቲካ እስረኞች እንዲሁም በአገሪቱ ውስጥ ስላለው የፕሬስ አፈና ያላቸውን ስጋት ገልጠዋል።

ያለ ፕሬስ ጠንካራ የሆነ ዲሞክራሲያዊ ስርአት መገንባት እንደማይቻል የገለጡት ሮይስ፣ በአገር ደህንነትና ሽብርተኝነትን በመዋጋት ስም የፕሬስ መብቶች እየታፈኑ ጋዜጠኞችም እየተዋከቡ ነው ብለዋል።

በኢትዮጵያ የሚገኙ የፖለቲካ እስረኞች ለፍርድ ቢቀርቡም፣ የፍርድ ሂደቱ አለማቀፍ መስፈርቶችን ያሟላ አለመሆኑ እና በእስረኞች ላይ በቴሌቪዥን ፕሮፓጋንዳ መሰራቱ ጉዳዩ ፖለቲካዊ መሆኑን የጠቀሱት አሜሪካዊው ባለሥልጣን ኢትዮጵያ ጠቃሚ የሆነ የኢኮኖሚ እድገት አስመዝግቢያለሁ እያለች ብትሆንም፣ በፕሬሱ ላይ የሚታየው አፈናና የፍርድ ቤት ነጻነት አለመኖር እነዚህን አወንታዊ ለውጦች እንደሸፈናቸው ባለስልጣኑ ተናግረዋል።

ሴናተር ማርክ ቤጊች በበኩላቸው የኦባማ አስተዳዳር በደህንነትና በኢኮኖሚ ሰበብ ከአምባገነን መንግስታት ጋር መወደጀቱ ለአሜሪካ ዘላቂ ጥቅም ጎጂ መሆኑን ከሰሜን አፍሪካ ቅርብ ተመክሮ መረዳት ይቻላል ብለዋል።

ኢትዮጵያውያን የመለስን በቡድን 8 አገራት ስብሰባ ላይ መጋበዝ በተመለከተ ያሳዩት ተቃውሞ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚፈጸመው የሰብአዊ መብት ጥሰት የአሜሪካ ፖለቲከኞች ለጉዳዩ ትኩረት መስጠት መጀመራቸውን ያሳያል የሚሉ አስተያየቶች ቀርበዋል።

ግዜ

ግንቦት 7 ዜና

## ወያኔ የአፋርን ህዝብ እርስ በርሱ በማጋጨት ላይ መሆኑ ተዘገበ። 95 ንጹሃን ሲገደሉ ከ60 በላይ ታስረዋል

የአፋርን ህዝብ ከሰፈሩበት የአዋሽ ተፋሰስ በሃይል በማፈናቀል መሬታቸውን ለሸንኮራ ልማት በመሸጥ ላይ የተሰማራው የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ ከህዝብ የደረሰበትን ተቃውሞ ለመከፋፈል ሲል ብሄረሰቡን በወረዳ ከፋፍሎ እርስ በርስ ለማጋደል በዘመቻ ላይ መሆኑን ለግንቦት 7 ቅርበት ያላቸው ምንጮች ገለጹ።

እንደ ምንጮቻችን መረጃ የአሞሌና የጨው ምርት እምብርት በሆኑት ሁለት አጎራባች የባራሄሌና አፍቤራ ወረዳዎች ውስጥ የሚኖሩትን የአፋር ጎሳዎች እርስ በርስ በማጋጨትና የአፋር ህዝብን ከመሬቱ ላለመፈናቀል እያሳየ ያለውን የተጠናከረ ተቃውሞ ለማዳከም ሲባል ቀደም ሲል በአፍቤራ ወረዳ ሥር የሚተዳደረውን አፍአሌና ሃመድዔላ የተባሉትን ቀበሌ ወደ ባራሄሌ ወረዳ እንዲጠቃለል በማሻጠር ህዝቡ ግጭት ውስጥ እንዲገባ እየተደረገ ነው።

የአፍቤራን የጨው ሃብት በብቸኝነት እያምረተ ሃብት በማጋበስ ላይ የሚገኘው ጸጋዬ የተባለ ግለሰብ ህዝብን በማከፋፈሉ ተግባር ውስጥ ተዘፍቆል የሚሉት ምንጮች በባራሄሌ በኩል ጄነራል ሳአሬ የተባለ የህወሃት የቀድሞ ታጋይ ግጭቱን እየቆሰቆሰ መሆኑን አጋልጠዋል።

ከአሁን ቀደም በገዋኔና በቡሪሙዳይቱ ወረዳ የሚኖሩትን ሁለት የአፋር ጎሳዎች በተመሳሳይ ተንኮል በማጋጨት 95 ንጹሃን ዜጎች መሞታቸውንና ከ60 በላይ የአፋር ወጣቶች ከመቀሌ 45 ኪሎሜትር ርቀት ላይ በሚገኝ ቆላማ ሥፍራ መታሰራቸው ታውቆአል።

በእስር ላይ የሚገኙ ወጣቶች እስካሁን ድረስ በቤተሰቦቻቸው እንዳይጎበኙና ምንም አይነት እርዳታ እንዳይቀበሉ ራቅ ያለ ቦታ ላይ በመታሰራቸው የአካባቢው ህዝብ እስር ቤቱን የአፋር ጓንታናሞ ቤይ እያሉ እንደሚጠሩት ተያይዞ የደረሰን ዜና ያስረዳል።

ወያኔ በአፋር ህዝብ ላይ ከሚፈጽማቸው ሰቆቃዎች በተጨማሪ አንዱን ጎሳ በሌላው ላይ በመቀስቀስ ደም እያቃባ መሆኑን መላው የኢትዮጵያ ሕዝብና የተቀረው የአለም አቀፉ ህብረተሰብ እንዲያውቅላቸው የአካባቢው ህዝብ ምኞት መሆኑን መረጃውን ያቀበሉን ምንጮች ገልጸዋል።

ግንቦት 7 ወያኔ በህዝባችን ላይ የሚፈጸመውን ግፍ ለማስቆም ሁሉም ተባብሮ እንዲነሳ የሚወተውተው በአፋር ህዝብ ላይ እየደረሰ ያለው ዘግናኝ እልቅት ጭምር እንዲቆም ለማስቻል እንደሆነ ይታወቃል።

## የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትሩን ስብሰባ ላይ የዘለፈችው ሙስሊም ወጣት፤ በደህንነቶች በደረሰባት አሰቃቂ ድብደባ ህይወቷ ማለፉ ተነገረ

ይህ አሳዛኝ ዜና ይፋ የሆነው፣ የብዙሀኑ ሙስሊም አስተባባሪ አካል የሆነው "ድምፃችን ይሰማ" ኮሚቴ፦ አሳዛኝ የግፍ ዜና"በሚል ርዕስ ያሰራጨው መረጃ ነው።

በቅርቡ የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር የሙስሊሞችን ጥያቄ በተመለከተ ከየክፍለ-ከተማው ሰዎችን በመምረጥ ስብሰባ አካሂዶ እንደነበር ያወሳው ኮሚቴው፤ በዚሁ ስብሰባ ላይ ከኮልፌ ክፍለ-ከተማ ሁለት ወንዶች እና ፍርዶስ የተባለች ወጣት ሴት መሳተፋቸውን አመልክቷል።

ስብሰባውን ሲመራ የነበረው ሚኒስትሩ ዶክተር ሽፈራው ተክለማርያም ብዙሀኑን ሙስሊም ያስተባብሩ ዘንድ በተመረጡት የኮሚቴ አባላት ላይ አስፀያፊ እና ድንበር ዘለል ንግግሮችን ሲደጋግም በመደመጡ፤ የሰውዬውን ዘለፋና ስድብ መሸከም ያቃታት እህት ፍርዶስ የእልህ ሲቃ እየተናነቃት ሚኒስትሩን ዘልፋ የስብሰባ አዳራሹን ለቅቃ መውጣቷን ከኮሚቴው ለኢሳት በሰጠው መረጃ ይፋ አድርጎአል።

ከአዳራሹ ወጣታ በ አቅራቢያው ወዳቆመቻት ቶዮታ ቪትዝ የግል መኪናዋ በመግባት ወደመጣችበት ለመመለስ መንቀሳቀስ እንደጀመረች በሁለት ላንድክሩዘር መኪኖች የሞሉ ደህንነቶች ተከትለው በማስቆም እሷንም፤ መኪናዋንም ይዘው መሰወራቸውን ኮሚቴው አጋልጧል ብሎአል ኢሳት።

"ከዚያም እህታችን ፍርዶስን በሚያሰቅቅ እና በሚዘገንን መልኩ በኤሌክትሪክ "ሾክ"እያደረጉ አቃጠሏት" ያለው ኮሚቴው፤ በዚህም ምክንያት ወጣት ፍርዶስ ወዲያውኑ መናገርም፤መንቀሳቀስም ማቆሟን ገልጿል።

እንደ ድምፃችን ይሰማ መግለጫ፦-ደህንነቶቹ በፍርዶስ ላይ የተጠቀሰውን የጭካኔ ድርጊት ከፈፀሙባት በሁዋላ ከነ መኪናዋ መኖሪያ ቤቷ በሯ ላይ ጥለዋት ሄደዋል። (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## ልምድ ሊቀሰምበት የሚገባ አኩሪ ተግባር!

ቀኑ ግንቦት 10፣ 2004 ዓም ነበር። ቦታው አሜሪካ፣ ዋሽንግተን፤ ጋባዡም ፕሬዚዳንት ኦባማ ነበሩ። ጉዳዩ የዓለም የግብርና ልማትና የምግብ ዋስትና ስለማረጋገጥ ነው። ስብሰባው ተጀመረ። መለስ ዜናዊ እንደተለመደው ውሸቱን በስታትስቲክስ ጀመረ። ሆኖም ግን በድንገት "መለስ ዜናዊ አምባገነን ነው!!!" የሚል ታላቅ ድምጽ ንግግሩን አቋረጠው።

ኢትዮጵያ ውስጥ፣ በፓርላማም ሆነ ከፓርላማ ውጭ መለስ ዜናዊ እንደፈለገ ሲዘባርቅ ኖሯል። የፊት ለፊት ተቃውሞ እንዳይኖር አድርጓልና ትናንት የተናገረውን ዛሬ መካድ አያሳፍረውም። መለስ ለራሱም ለሌሎችም ውሸትን እየመገበ፤ መሬት ላይ ጨርሶ ስለሌለ እድገት እና ስሌት አጋኖ በማውራት ተወዳዳሪ የሌለው ታላቅ የውሸት ባለሙያ ሆኗል።

መለስ ዜናዊ የተሳተፈባቸው ስብሰባዎችን በአንክሮ የተከታተለ ሰው የሚያገኘው ዘረኛ፣ ትዕቢተኛ፣ ዋሾ፣ ተራቢ፣ ተሳዳቢ የሆነውን ሰው ነው። መለስ በእንዲህ ዓይነት ስብዕና ነው አዋራጅ የሆነውን ዘረኛ አምባገነን ሥርዓትን ገንብቶ እየገዛን ያለው። እንዲህ ዓይነቱን ብልሹ ሥርዓት ለመገንባት የመለስን ያህል የተበላሹ ባህሪያት ባለቤት መሆን ይፈልጋል። መለስ እና የሚመራው ሥርዓት አንድ አካል፤ አንድ አምሳል የሆኑት ለዚህ ነው።

መለስ በተሳተፈባቸው ጉባኤዎች ኢትዮጵያዊያን በተደጋጋሚ ተሸማቀናል፤ አፍረናል። መለስ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊያንን እንዳሸማቀቀ ሊሸማቀቅ፤ እንዳዋረደ ሊዋረድ ይገባዋል። እስከ ግንቦት 10 ቀን 2004 ዓም ግን ይህ ሊሆን አልቻለም ነበር። ለዚህም በርካታ ምክንያቶች ነበሩ

1. መለስ የሚሰበሰበው ከአሽከሮቹና ከምስለኔዎቹ ጋር ነው። በዘር መስፈርት የሰበሰባቸው አሽከሮቹ ጌታቸው የሚለው ነገር ባይገባቸውም የሚያጨበጭቡ ናቸው። ከተለያዩ አካባቢዎች በጥቅም የሰበሰባቸው ምስለኔዎች ደግሞ መለስ በሚለው ባይስማሙም ለጥቅማቸው ሲሉ ማጨብጨብን የሚመርጡ ናቸው።
2. ህሊና ያላቸው ጥቂት ሰዎች ቢገኙም የሚናገሩበት እድል ተነፍገው ቆይተዋል። በፓርላማ፣ ለምሳሌ፣ መለስ የመጨረሻ ተናጋሪ ነው። እሱ አይነኬ እና ሙሉ በኩልሄ ነው።
3. በውጭ አገራትም ቢሆን እያወቁ ውሸት የሚጋቱለት ለጋሽ መንግሥታትና ድርጅቶች አሉ። እነዚህ መንግሥታትና ድርጅቶች የመለስ የስታትስቲክ ቁጥሮች ውሸት መሆናቸውን ያውቃሉ። በእርዳታ ስም የሚልኩት ገንዘብ ወደ መለስ እና ዘመዶቹ የግል ሂሳብ እንደሚዛወር መረጃዎች አሏቸው። ያም ሆኖ ግን የመለስ ዜናዊን የውሸት ቁጥሮች እየሰሙ በገንዘባቸው ውጤት የማየት ጉጉታቸውን ይወጣሉ።

ስለሆነም መለስ እንደቀጠፈና እንደዘለፈ፤ ኢትዮጵያዊያን እንደተሸማቀቁ ግንቦት 10 ቀን 2004 ዓ.ም. ደረሰ። ይህ ቀን ግን ከወትሮው የተለየ ሆነ። በዚህ ቀን ሲያሸማቅቅ የኖረው መለስ ተሸማቀቀ፤ ሲያዋርድ የነበረው መለስ ተዋረደ።

በግብርና ልማትና የዓለም የምግብ ዋስትና ስለማረጋገጥ ለመምከር የተጠራው ስብሰባ ተጀመረ። ይህ ስብሰባ የመንግሥታት፣ የዓለም ዓቀፍ ድርጅቶች መሪዎች እና ዓለም ዓቀፍ ዝና ያላቸው ባለሙያዎች የታደሙበት ነው። መለስም እንደተለመደው ውሸቱን በስታትስቲክስ ጀመረ። በድንገት "መለስ ዜናዊ አምባገነን ነው!!!" የሚል ታላቅ ድምጽ ንግግሩን አቋረጠው።

ይህች ቀን የመለስ ዜናዊ አልነበረችም። በአዳራሹ ውስጥ የተሰማው ያ ታላቅ ድምጽ የተሰብሳቢውን ትኩረት ሳበ። ተናጋሪውም በበለጠ ጉልበት ቀጠለ ...

*መለስ ዜናዊ አምባገነን ነው!!! መለስ ዜናዊ አምባገነን ነው!!! ነፃነትን እንፈልጋለን!!! መለስ በስብዕና ላይ ወንጀል የፈፀመ ነው!!! መለስ ወንጀለኛ ነው!!! ምግብ ያለ ነፃነት ምንም ማለት አይደለም!!! እስክንድር ነጋንና ሌሎችን የፖለቲካ እስረኞች ይለቀቁ!!! ነፃነት እንሻለን!!! ነፃነት እንፈልጋለን!!! መለስ አምባገነን ነው!!! ነፃነት እንፈልጋለን!!! ነፃነት!!! ነፃነት!!! ነፃነት!!! ነፃነት!!!*

መለስ ዜናዊ ደነገጠ፤ ዓይኖቹ በድንጋጤ በልጥጠው ታዩ። ቀጥሎ ግን ፍርሃት ሰውነቱን የወረረው መሆኑ ታየ። መለስ በመሸማቀቅ አንገቱን ደፋ።

ተናጋሪው የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን (ኢሳት) ጋዜጠኛ የሆነው አቶ አበበ ገላው ነበር። አቶ አበበ ገላው ታፍኖ ለቆየው ሕዝብ አንደበት ሆኖ ተናገረ። በአበበ ተግባር ኢትዮጵያዊያን ኩራት ተሰምቷቸዋል። ከኢትዮጵያም አልፎ በርካታ ዓለም ዓቀፍ ሚዲያዎች የአቶ አበበ ገላውን ድፍረት በማድነቅ ጽፈዋል።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄም አቶ አበበ ገላን "አበጀህ!!!" ይላል። ግንቦት 7 ከዚህ ድርጊት ልንቀስማቸው የሚገቡ ነገሮች አሉ ብሎ ያምናል።

1. በርካታ ሕዝብ በተሰበሰበት ዓለም ዓቀፍ ጉባኤ ውስጥ አበበ መለስ ዜናዊን "አምባገነን፣ ወንጀለኛ" ብሎ ከጠራ በኋላም አለመታሰሩ፣ አለመከሰሱ፣ አለመጎንተሉ ነፃነት ባለበት አገር የዜጎች መብት ምን ያህል እንደሆነ አንድ ተጨባጭ ማስረጃ ነው። እንደ መለስ ዜናዊ ህግ ቢሆን ኖሮ የአቶ አበበ ድርጊት "ሽብርተኛ" አስብሎ ሞት ያስፈርድ ነበር። በመለስ ህግ መሠረት ፎቶ ማንሳት እንኳን "ሽብርተኛ" እንደሚያስብልና የ14 ዓመታት ጽኑ እስር እንደሚያስፈርድ በወ/ት ርዕዮት ዓለሙ በደረሰው የምናውቀው ነው።
2. የአቶ አበበ ድርጊት "እንዴት ነው ወያኔን መታገል የምችለው?" ብለው ለሚጠይቁ ወገኖች ምላሽ የሰጠ እና በተገኘው አጋጣሚና መንገድ ሁሉ መታገል እንዳለብን የሚያስገነዝብ ነው። በምርጫ 97 ማግሥት በአውሮፓ ኮሚሽን የስብሰባ አዳራሽ ውስጥ የቅንጅት ደጋፊዎች መለስን ካዋረዱ ወዲህ ይህ የመጀሪያው ፋና ወጊ እርምጃ ነው። ነውረኛን ማስነወር ተቀባይነት ያለው የትግል ስልት ነው።
3. ይህ ድርጊት "እኔ ብቻዬን ምን ለውጥ አመጣለሁ" ለሚሉ ወገኖቻችን ተጨባጭ ምላሽ የሰጠ ነው። አቶ አበበ ብቻውን ለዚያውም ድምጹን ብቻ ተጠቅሞ የፈፀመው ድርጊት ምን ያህል ሕዝብን እንዳነቃነቀ ልብ ይሏል።

ይህ ድርጊት የሚዲያ ሚና ታላቅነት አጉልቶ ያሳየ ነው። በሚዲያ ሰበብ ነው አቶ አበበ አዳራሹ ውስጥ የገባው። አቶ ግርማ ደገፋን የመሰለ የሰለጠነ የቀረፃ ባለሙያ ስለነበረ ነው የአቶ አበበን ድምጽ በመለስ ዜናዊ ያስከተለውን መደናገጥ ማየት የቻልነው። በመጨረሻም ኢሳትን የመሰለ ነፃ ሚዲያ ስላለ ነው ዜናው ከመቅጽበት የተሰራጨው።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ይኸ መልካም ጅማሮ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት ይላል። ትግላችን ሁለገብ ነው። ነፃነት የጠማው ህዝብ የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አምባገነን አገዛዝን በሁሉም ግንባሮች ገጥሞ እየተፋለመው ነው። ፍልሚያው ይበልጥ እየፋመ፣ እየከረረና እየመረረ ነው። ዘረኝነትንና አምባገነንነትን ለመቅበር ሁላችንም እንነሳ።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

## በሰሜን አሜሪካ የመለስ ዜናዊ ተጠሪ የሆነው ግርማ ብሩ በቡድን 8 ስብሰባ ላይ የጌታውን ቆሌ የገፈፈውን . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ዜናውን ለማስተባበል ሲሉ የተለመደውን ትንሽነታቸውን የሚያረጋግጥና ለህዝብ ስቃይ ደንታ ብስነታቸውን የሚያጋልጥ የውሸት መግለጫ እየሰጡ ነው።

በመለስ ዜናዊ የሚመራው የወያኔ አገዛዝ ያስመዘገበው የምግብ ዋስትና የኢትዮጵያን ገጽታ ቀይሮታል በማለት የአይጥ ምስክርነት የሰጠው ግርማ ብሩ አለቃው መለስ ዜናዊን ቆሌ የገፈፈ የዋሽንግተኑ ተቃውሞን በማድበስበስ ከቁጥራቸው ማነስ የተነሳ ድምጻቸው የትም ቦታ ያልተሰማን የወያኔ ደጋፊዎች የድጋፍ ሰልፍ ለኢትዮጵያ ህዝብ ለማሳመን ሲል አለቃው መለስ ዜናዊ በአንድ ወቅት በሩዋንዳ የዘር እልቂትን አነሳስቶአል ከሚባለው ሬዲዮ መሊኮሊን ጋር በማመሳሰል የከሰሰውን የአሜሪካንን ድምጽ ሬዲዮ ሪፖርት በዋቢነት ሲጠቅስ ተስተውሎአል።

በዘንድሮው የቡድን 8 ስብሰባ ላይ የመለስ ዜናዊ መገኘት በተቃውሞ ጎራ ለተሰለፈው የኢትዮጵያ ህዝብ እንደ ድል ይቆጠራል የሚሉ በርካታ የፖለቲካ ተንታኞች ሲኖሩ፤ የሚሰጡት ምክንያትም ትላልቅ የአሜሪካ ባለሥልጣናትና ከርሱ ጋር ከአፍሪካ ተጋብዘው የመጡ የሌሎች አገሮች ፕሬዝዳንቶች ባሉበት ቆሌውን የገፈፍና አመዱን ቡን ያደረገ ተቃውሞ ከነበረበት የስብሰባ አዳራሽ ውስጥና ውጪ የገጠመው መሆኑን እንዲሁም ከምርጫ 97 ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ ትላልቅ የአለም የዜና አውታሮች ዜናውን ተቀባብለው መዘገባቸውን እንደማስረጃ ይጠቅሳሉ።

ይህ በዚህ እንዳለ ግርማ ብሩ አሜሪካን አገሪ የሚገኙትን የወያኔ ደጋፊዎች አሰባስቦ ለመለስ ዜናዊ ክብር አዘጋጅቶት የነበረው የክብር ግብዣ ላይ የተጠበቁት ያህል ሰዎች አለመገኘታቸውና መለስ ዜናዊ እራሱ በደረሰበት ተቃውሞ አፍሮና በተዘጋጀለት ግብዣ ላይ ለመገኘት ወኔ አጥቶ እንደተመለሰ ለማወቅ ተችሎአል።

ከመለስ ዜናዊ ጋር እራት ለመቋደስ የተጠሩት የወያኔ አፍቃሪዎች በተጠሩበት አዳራሽ ውስጥ ቁጭ ብለው በመጠባበቅ ላይ በነበሩበት ወቅት ግርማ ብሩ ፈራ ተባ እያለ ጠቅላይ ሚንስትራቸው ለአስቸኳይ ሥራ ወደ አገር ቤት መመለሱን መርዶ ሲናገር በቦታው የነበሩት ሁሉ መደናገጣቸውን የገለጹት ምንጮች ቀደም ተብሎ በተያዘለት ግብዣ ላይ ያለመገኘቱን የፈጠረው በዚህኛው ጉዞው የገጠመው ቅሌት እንደሆነ ሁሉም ያምናሉ ብለዋል።

ግርማ ብሩ በወያኔ አገዛዝ በሙስና ከተዘፈቁት ባለሥልጣናት አንዱ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ልጆቹን በአሜሪካን አገር እጅግ ውድ በሚባል ዩኒቨርሲቲ ውስጥ እየከፈለ ማስተማሩና በብዙ ሚሊዮን ወጪ ዘመናዊ ቪላዎችን አገር ቤት ውስጥ ማሰራቱንና በስሙ ፈረንጅ አገር ገንዘብ እያከማቸ መሆኑ ካሁን በፊት መዘገባችን ይታወሳልል።

## ብሶት የወለደው ህወሃት/ኢሕአዴግ ያመጣብን ውርደት

ብሶት ወለደኝ ያለው ህወሃት/ኢህአዴግ አገራችንን ከተቆጣጠረ ግዜ ጀምሮ በአገሪቷ ላይ የደረሰውን ውርደት ቆጥረን አንጨርሰውም። ህወሃት አገሪቷን ከተቆጣጠረ ብኋላ ነው ከአገሪቷ ብሄራዊ ባንክ ውስጥ ለክፉ ግዜ የተቀመጠ ወርቅ ተሰርቆ በባሊስትራ ተተክቶ የተገኘው። ህወሃት አገሪቷን ሙሉ በሙሉ ከተቆጣጠረ በኋላ ነው ከ11.8 ቢሊዮን ዶላር በላይ በውጭ አገራት ባንኮች ውስጥ ተደብቆ መገኘቱ የተሰማው። በዚህ በህወሃት ዘመን ነው 9 ሚሊዮን ኪሎ ግራም ቡና ከአገሪቷ ጠፋ የተባለው እና የአንድ ኪሎ ቡና ከ180 ብር በላይ የገባው።ህወሃት/ኢሕአዴግ አገሪቷን ከተቆጣጠረ በኋላ ነው አገሪቷ ክብሯ የተዋረደው። ዜጎቿም ለስደትና ለጉስቁልና የተዳረጉት።

አገራችን ትልቅ ነበረች። ለትልቅነቷ በርካታ ማስረጃዎችን መጥቀስ እንችላለን።ዛሬ ያሉ ታላላቅ አገሮች ከመኖራቸው በፊት ኢትዮጵያ ባለዝና አገር ነበረች።ስማቸው የገነኑ ፈላስፎች፤ ምሁራንና ሌሎች በርካታ ታዋቂ ሰዎች ነበሩባት። በመጽሃፍ ቅዱስ ውስጥ ስመ ጥር የሆነው ዮቶር ኢትዮጵያዊ ነበር።

ሙሴ እስራኤላዊያንን ከግብጽ ምድር እየመራ ቀይ ባህርን ተሻግሮ በኢትዮጵያ በኩል ሲያልፍ ከኢትዮጵያዊ አማቹ ጋር ተገናኘ።በዚያን ወቅት ሙሴ አስተዳደራዊ ጉዳዮችን በመምራት በኩል ብርቱ ችግር ነበረበት። አማቹ ዮቶርም ይህን ችግር በመስማቱ ሙሴ እንዴት አድርጎ ህዝቡን ማስተዳደር እንዳለበት አስተማረው። ሙሴም የአማቹን ትምህርት ተቀብሎ በተግባር በማዋሉ በአስተዳደር በኩል የነበረበት ችግር ሊቃለልለት ችሏል። ከዚያ በኋላ ፍትሃዊ አስተዳደር በመስፈኑም በህዝቡ መካከል የሚነሱ ችግሮች በተቀላጠፈ ሁኔታ መልስ ያገኙ ጀመር።

ዮቶር ለሙሴ ያስተማረውን አስተዳደራዊ ሥርዓት የተማረው በወቅቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ከነበረው የአስተዳደር ሥርዓት ነበር። ከዮቶር በፊት በኢትዮጵያ ውስጥ አገሪቷን በወግና በማእረግ ሲመሩ የነበሩ ነገስታት ነበሩ። ኢትዮጵያም የገነነች እና የታፈረች አገር ነበረች። ዜጎቿም በየሄዱበት ተከብረው አንገታቸውን ቀና አድርገው በኢትዮጵያዊነታቸው ኮርተው እና ደስ ብሏቸው የሚኖሩ ነበሩ። እስከ ቅርብ ግዜ ድረስ ኢትዮጵያዊ በሚሄድበት አገር ሁሉ መታወቂያ ሳይጠየቅ ይገባ ነበር። ኢትዮጵያዊ ነኝ ማለት ብቻ በቂው ነበር።
ዛሬስ ?!

ብዙ ሰዎች የዛሬ እጣ ፈንታችንን ባሰብን ቁጥር አንገታችንን ደፍተን እንተከዛለን።ዛሬ ኢትዮጵያ ፍትህ የተዋረደባት አገር ሁናለች።ዛሬ አብዛኛው ዜጎቿ ስደተኛና በገዛ አገራቸውም ባይተዋር ሁነዋል።ዛሬ ወልደው ዘር የሚተኩ ሴቶች ልጆቿ ለአረቦች በገንዘብ የሚሸጡ ሁነዋል።ህግም በመለስ ዜናዊ ስሜት በመተካቱ ፍትህ ተዋርዳለች።

በህወሃት/ኢሕአዴግ ፍትህ ተዋረደ የምንልበትን ምክንያት ከብዙው አንዱን ብቻ እናሳያችኋለን። ይህንንም በታሪክ ተመዝግቦ የተቀመጠውን ያገኘነው የቃሊትው መንግስት ከሚል መጽሃፍ ላይ ነው ።

በ1997 ዓ.ም በተደረገ ምርጫ ህወሃት/ኢሕአዴግ መሸነፉ እውነት ቢሆንም ህወሃት እምቢ ብሎ ህዝቡ የመረጣቸው መሪዎች በሙሉ በዘር ማጥፋት እና በአገር ክህደት ወንጀል ከሶ የሞት ፍርድ ማስፈረዱን እናውቃለን። መቸስ እንዲህ ዓየነት ነውር በኢትዮጵያ ውስጥ በመፈጸሙ ዓለምም ጉድ ማለቱን ሰምተናል።

መለስ ዜናዊ በሞት እንዲቀጡሉት በፈለገው ዜጎች ላይ ካቆመው ምስክሮች መካከል የአንዱን ሁኔታ ተመልከቱና አገራችን በምን ዓይነት ውርደት ውስጥ እንዳለች ራሳችሁ ፍረዱ።

የመስካሪው ስም አዳነ በቀለ ይባላል። አዳነ የእናቱ ስም ስላስ የሚባል ሲሆን በአዲስ አበባ የቀበሌ ሊቀመንበርም ነው።

አሁን አዳነ ለእውነት ሳይሆን ለመለስ ዜናዊ ሊፈርዱለት በተቀመጡ “ዳኞች” ፊት ለምስክርነት ቀርቧል።

*ዳኛ፡* አቶ አዳነ ምን ልትመሰክር መጣህ ?

*አዳነ፤* በአገር ላይ ሽብር እንዲፈጠር የሚያነሳሳ ወረቅት በትን ብለውኝ መበተኔን ልመስክር መጣሁ።

*ዳኛ፡* የት የት በተንክ ?

*አዳነ፡* አዲሱ ገበያ አካባቢ።ታክሲ ውስጥ።ሁሉም ቦታ በትኜአለሁ።

*የተከሳሽ ጠበቃ፡* ወረቀቱን ከሰጠሃቸው ሰዎች መካከል እስኪ የአንድ ሰው ስም ጥራ፤

*አዳኑ፡* አላስታውስም።

*የተከሳሽ ጠበቃ፡* መልካም ፤እስኪ አንተ ለማታውቀው ሰው የሰጠህበትን አንድ አጋጣሚ ብቻ ንገረን፤

*አዳነ፤* ታክሲ ውስጥ ለአንድ ሰው ሰጥቼአለሁ።

*የተከሳሽ ጠበቃ፡* ታክሲው ከየት ወደየት ይሄድ ነበር?

*አዳኑ፡* ከአዲሱ ገበያ ወደ ፒያሳ

*የተከሳሽ ጠበቃ፤* እንዴት ለዚያ ሰው ደፍረህ ሰጠህ?

*አዳኑ፡* ነጻነት የተባለ ጋዜጣ ሲያነብ ስላየሁት እኔም በታክሲው ተሳፍሬ አብረን እየተጓዝን በወቅታዊ የአገር ጉዳይ ላይ ወሬ ጀምረን ስለተግባባን ወረቀቱን ሰጠሁት።

*የተከሳሽ ጠበቃ፡* ሰውየው የት ወረደ?

*አዳኑ፡* እኔ ቀድሜ ስለወረድኩ የት እንደወረደ አላውቅም።

*የተከሳሽ ጠበቃ፡* አንተ የት ወረድክ?

*አዳኑ፡* አዲሱ ገበያ።

አዳነ የእነመለስ ዜናዊ ምስክር ነው። ከአዲሱ ገበያ ተሳፍሮ ሲጓዝ ቆይቶ እዚያው አዲሱ ገበያ የወረደው ምስክር ቃሉ ጸንቶ በንጹሃን ዜጎች ላይ የሞት ፍርድ እንዲፈረድ ተደርጓል። ፍትህ ተዋረደ የምንለው ይህን ስናይ ነው። እንዲህ ዓይነት ነውር ነገር በአገራችን መፈጠሩም በእጅጉ ያሳዝነናል።

አዳነን ምስክር አድርገው ያቀረቡት አቃብያነ ህጎችን እዚህ ላይ ለማስተዋወቅ እንወዳለን። 1ኛ. ሽመልስ ከማል 2ኛ. አብርሃ ተጠምቀ 3ኛ. ሚካኤል ተክሉ ናቸው። ሁለቱ ትግሬን ነጻ አወጣለሁ የሚለው ህወሃት አባላት ሲሆኑ የመጀመሪያው ሽመለስ ከማል በአሁኑ ሰዓት ሹመቱ አድጎለት የመለስ ዜናዊ አፈ ቀላጤ ሁኖ በአሸባሪነት ከተፈረጁ ግለሰቦች ጋር መነጋገር በአሸባሪነት እንደሚያስከሥሥ የዛተው ነው።

እንዲህ ዓይነቱን የሃሰት ምስክር አዘጋጅቶ በንጹሃን ዜጎች ላይ የሞት ፍርድ የሚፈርድ አገዛዝ በአገራችን ራስ ተቀምጦ እያየን ዝም አንልም። ፍትህ ከአዋራጆቿ እጅ ወጥታ ቦታዋን እስከምትይዝ ድረስ ግንቦት ሰባት ንቅናቄ የጀመረውን ትግል አጠናክሮ ይቀጥላል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ ይሁን !!!**

**እግዚአብሄር አገራችንን ይባርክ !!!**

## የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትሩን ስብሰባ ላይ የዘለፈችው ሙስሊም ወጣት፤ በደህንነቶች በደረሰባት አሰቃቂ ድብደባ . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

በሁኔታው ከፍተኛ ድንጋጤ ላይ የወደቁት የፍርዶስ ቤተሰቦች ልጃቸውን ለመታደግ ሩጫ መጀመራቸውን የጠቀሰው ኮሚቴው፤ሆኖም የደረሰባት ጉዳት እጅግ ከባድ በመሆኑ ጥራታቸው ሁሉ ከንቱ መቅረቱን ነው ያመለከተው።

በሆነው ነገር ልባቸው በሀዘን የደማው የፍርዶስ አባት የልጃቸውን ህይወት ለማትረፍ ከፍተኛ ወጪ በማውጣት ለህክምና ወደ ሳዑዲ ዐረቢያ ይዘዋት ቢሄዱም፤ ደህንነቶቹ ባደረሱባት የኤሌክትሪክ ቃጠሎ በርካታ አካሎቿ ከጥቅም ውጪ በመሆናቸው ወጣት ፍርዶስ እስከወዲያኛው ተሰናብታለች።

የከፋው አሳዛኝ ነገር የወጣት ፍርዶስ ህይወት ማለፉን ተከትሎ ወላጅ እናቷ በደህንነቶች ታፍነው መወሰዳቸው ነው ይላል ኮሚቴው ወላጅ እናቷን አፍነው የወሰዷቸውም የፈፀሙት አሰቃቂ ግፍ እንዳይሰማባቸው ለማድረግ በማሰብ ነው ብሎ እንደሚያምን የድምጻችን ይሰማ ኮሚቴ ገልጿል።

መምህር የኔሰው ገብሬ፡-”ፍትህ በሌለበት አገር መኖር አልፈልግም”በማለት ራሱን ማቃጠሉን ተከትሎ የደህንነት አባሎች፡- ”መረጃ እንዳትሰጥ”በሚል እህቱን በመኖሪያ ቤቷ አፍነው ማስቀመጣቸው ይታወሳል።

ወጣት ፍርዶስ እሷን እና ጓደኞቿን እላፊ እየተናገሯቸው የነበሩትን የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትሩን በንዴት በመዝለፏ ሳቢያ በኤሌትሪክ ሾክ እየተደረገች እንድትሞት መደረጉን የሰሙ እትዮጵያውያን፤ ሰሞኑን ጋዜጠኛ አበበ ገላው፡- መለስ ዜናዊን ያን ያህል በአለም አቀፍ መድረክ ሲያዋርድ ኢትዮጵያ ውስጥ እየተካሄደ ባለ ስብሰባ ላይ ቢሆን ኖሮ ምን ሊያደርገው ይችል እንደነበር መገመቱ ቀላል ነው ብለዋል። ኢሳት የሟቹዋን ቤተሰቦች ለማነጋገር አደረገው ጥረት እናዳልተሳካና የወያኔ ባለሥልጣኖችንም በጉዳዩ ዙሪያ የሰጡት አስተያየት እንደሌለ ዘግቧል።

## ወያኔ በኦሞ ሸለቆ በሚኖሩ የሱሪ ና የቦዲ ብሄረሰብ አባላት ላይ እጅግ ዘግናኝ የሆኑ ግፎች. . . (ከገፅ 4 የዞረ)

በሱሪዎች ላይ የሚደርሰው ግፍ ትንሽ ትንሽ የመገናኛ ብዙሀንን ማግኘት ሲጀምር፣ ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ በገበያ ቦታዎችና በመንገዶች ላይ እየተለቀሙ ወደ እስር ቤት በመጋዝ፣ ያለምንም ማስረጃና ያለምንም ምስክር ከ18 እስከ 25 አመት በሚደርስ እስር እንዲቀጡ ይወሰናል።

በአሁኑ ጊዜ በአራት ሻምበል የሚመራ ቁጥር ከ1 እስከ 2000 ሺ የሚደርስ ወታደር በተጠንቀቅ ቆሞ ከሱሪዎች ጋር ተፋጧል። ሱሪዎች ተቃውሞ የሚያነሱ ከሆነ ወታደሮች እርምጃ ለመውሰድ ዘግጁ ናቸው። በሱሪዎች ላይ እየደረሰ ካለው ግፍና ስቃይ ጎን በአካባቢው ባሉ የቦዲ ብሄረሰቦችም ላይ ተመሳሳይ ሰቆቃ እየተፈጸመ እንደሚገኝ ታውቆአል።

ወያኔ የአካባቢውን መሬት ለውጪ ባለሃብቶች ለማስረከብ በሀና እና ሰለማጎ ወረዳ የሚገኙ ቦዲዎች እና ቺረም የሚባሉት ጎሳዎች ወደ ሰፈራ ጣቢያዎች እንዲገቡ ትእዛዝ እንደሰጣቸው ሲታወቅ ሁሉም ግን አናደርገውም በማለታቸው በክልሉ ከተሰማራው ወታደራዊ ሃይል ጋር ተፋጠዋል ተብሎአል።

የአካባቢው መሬት ተመልሶ ሊተካ በማይችል ሁኔታ በውጭ አገር ኩባንያዎች እየወደመ ነው። በለምነቱ ከኢትዮጵያ በሁለተኛ ደረጃ የሚታወቅ ደቡብ ኦሞ በግዴለሽነት የእርሻ ስራ ሙሉ በሙሉ እየወደመ በመሆኑ፣ አካባቢውን ከጥፋት እናድነው ሲሉ የአካባቢው ሰዎች ጥሪ ያቀርባሉ።

## የኢሳት ጋዜጠኛ አበበ ገላው "መለስ ዜናዊ አምባነን ነው" ድምጽ ኢትዮጵያ ውስጥ ዝነኛ እየሆነ ነው፤ የወያኔ ሚዲያዎች ንዴታቸውን መቆጣጠር አቅቷቸዋል

ግንቦት 10 ቀን 2004 በዋሺንግተን በተደረገው ስብሰባ ውስጥ የኢሳት ቴሌቪዥን ጋዜጠኛ የሆነው አበበ ገላው በመለስ ዜናዊ ላይ ያሰማው የተቃውሞ ድምጽ ኢትዮጵያ ውስጥ በሰፊው እየተሰራጨ መሆኑን የግንቦት 7 ዘጋቢ ከአዲስ አበባ ገለጸ።

ፕሬዝዳንት ኦባማ በጠሩት አለም አቀፍ ስብሰባ ላይ መለስ ዜናዊ አፍሪካን አስመልክቶ ስለምግብ መረሃ ግብር በተለመደው የውሸት ስታቲስቲክስ የታጀበ ንግግር በማድረግ ላይ በነበርበት ወቅት ጋዜጠኛ አበበ ገላው ከመቀመጫው ብድግ ብሎ *"መለስ ዜናዊ አምባነን ነው!!! መለስ በስብዕና ላይ ወንጀል የፈፀመ ነው!!! መለስ ወንጀለኛ ነው!!! ምግብ ያለ ነፃነት ምንም ማለት አይደለም!!! እስክንድር ነጋንና ሌሎችን የፖለቲካ እስረኖች ይለቀቁ!!! ነፃነት እንሻለን!!! ነፃነት እንፈልጋለን!!! ነፃነትን እንፈልጋለን!!! መለስ አምባገነን ነው!!! ነፃነት!!! ነፃነት!!! ነፃነት!!! ነፃነት!!!"* እያለ በከፍተኛ ድምጽ መጮሁ ይታወሳል።

እራሱ ንጉስ በሆነበት ፓርላማ ውስጥ አይኑን እያጉረጠረጠ ሁሉንም በመዝለፍ ወደር የለሽ ጀግና መስሎ ለመታየት የሚሞክረው መለስ ዜናዊ በግንቦት አስሩ የዋሽንግተን ዲሲ ስብሰባ በገጠመው የተቃውሞ ድምጽ ክፉኛ ተደናግጦ ለደቂቃ ያህል አንገቱን በሃፍረት ደፍቶ ከመታየቱም በላይ በዙሪያው በተሸኮለኮሉ አጃቢዎቹ ትጥቅ ደፋርና ጀግና መስሎ ሲታይ የነበረበትን ገጽታውን በመግፈፍ ፈሪነቱን አደባባይ አውጥቶአል።

መለስ ዜናዊ ነጻ ጋዜጠኞችንና ነጻነት ናፋቂ ዘጎችን ሲያስር፤ ሲገድልና ሲያሰድድ ኖሮ ያለቦታው በተጠራበት አለም አቀፍ ስብሰባ ላይ የሚሰጠውን የውሸት ዲስኩር ከመዘገብ ወንጀሉን ማጋለጥ የተሻለ ተልዕኮ መሆኑን የተረዳው ጋዜጠኛ አበበ ገላው በወሰደ እርምጃ ከአገር ውስጥና ውጪ በርካታ ሰዎች የትግል ወኔያቸው ሲነቃቃ መለስን በጀግንነትና በአዋቂነት ሲያሞካሹ በኖሩት የወያኔ ተከታዮች ጎራ ትርምስ እንደተፈጠረ የዘገበው ዘጋቢያችን መለስ ዜናዊ በድንጋጤ አንገቱን የደፋበት ቪዲዮ አገር ውስጥ መሰራጨቱ እንደታወቀ በዩቱብ እንዳይታይ መዘጋቱን ፤ሆኖም ሰዎች በተለያየ መንገድ እየተቀባበሉት እንደሆነ ገልጾአል።

እንደዘጋቢያችን መረጃ በርካታ ወጣቶች በተለይ "መለስ ዜናዊ አምባገነን ነው" የሚለውን የኢሳት ጋዜጠኛ አበበ ገላውን የመጀመሪያ ዓረፍተ ነገር በሞባይል ስልካቸው ላይ በጥሪ መቀበያ ድምጽነት መጠቀም ጀምረዋል።

በአንፃሩ ደግሞ የወያኔ ሚዲያዎች በመለስ ዜናዊ ላይ የደረሰውን ቅሌት የፈጠረባቸውን ንዴት መቆጣጠር ተስኗቸዋል ተብሎአል። በሚሚ ስብሃት የባለንብረትነት ሸፋን የሚሰራው የወያኔ ኤፍ ኤም ራድዮ ባለፈው እሁድ ፕሮግራሙ በዲያስፓራና በአበበ ገላው ላይ የማያባራ ዘመቻ ከፍቷል።

መለስ በአበበ ገላው ድምጽ አልደነገጠም ለማለት የሚሚ ራድዮ መለስ ዜናዊ "በትግሉ ወቅት መድፍና ታንክ ተደግፈው መጽሃፍ ያነቡ ነበር" ብሏል።

ከጥቂት ወራት በፊት የቀድሞ የወያኔ አባል የነበሩት አቶ ገብረመድህን አርዓያ መለስ ዜናዊ ፈሪ የነበረ መሆኑን መግለፃቸው ይታወሳል። እንደ አቶ ገብረመድህን ገለፃ መሠረት መለስ የመራው ብቸኛው ኦፕሬሽን አድዋ ውስጥ ባንክ ለመዝረፍ የተንቀሳቀሱ ጊዜ ሲሆን መለስ ጥሎ በመጥፋቱ ኦፕሬሽኑ ሳይሳካ መቅረቱ፤ ብዙ የህዋህት ወጣቶችም መሞታቸው ይታወቃል።

ወያኔ በሚሚ ስብሃት ኤፍ ኤም ሬድዮ አማካይነት በዲያስራ ላይ ያለውን ምሬትም እየገለጸ ነው። "መርዘኛ ዲያስፖራ የእርጎ ዝምብ ነው" "መርዘኛ ዲያስፓራ መቸም ቢሆን ስልጣን አያገኝም" የሚሉና የመሳሰሉ ኃይለ ቃላት ሲሰሙ ነው እሁድ የታለፈው።

ከሁሉም በላይ አድማጭን ያስደመመው ግን የአበበ ገላውን ድርጊት በጠላት ወረራ ወቅት ኃይለሥላሴ በጄኔባ ንግግር ሲያደርጉ የጣሊያን ጋዜጠኞች ካደረጉት ጩከት ጋር ማመሳሰላቸው ነው። ይህ ንጽጽር የአበበ ድምጽ የፈጠረባቸው ድንጋጤ ጭንቅላታቸውን ነክቷል አሰኝቷል።

ሁኔታውን በአንክሮ የተከታተሉ ተንታኞች ከአበበ ድርጊት የምንማረው ትልቁ ቁምነገር አምባገነኖች ምን ያህል ፈሪዎች እንደሆኑ እና ተባብረው ከተነሳንባቸው በቀላሉ የሚደረመሱ መሆናቸውን ይላሉ።

## ዘረኛው መለስ ዜናዊን አንገት ያስደፋው ተቃውሞ በበርካታ አለም አቀፍ መገናኛ ብዙሃን ተዘገበ

በዘንድሮው የቡድን 8 አገሮች ላይ በፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ ተጋብዞ ወደ አሜሪካ ማቅናቱ በአፍቃሬ ወያኔና በነርሱ ሥር ባለው ሚዲያ እንደትልቅ ድል ሲናፈስለት የከረመው መለስ ዜናዊ ከኢትዮጵያዊያንና በአለም በታወቁ የመብት ተከራካሪ ድርጅቶች አንገት የሚያስደፋ ተቃውሞ የገጠመው ብቸኛ ሰው መሆኑ በተለያዩ አለም አቀፍ ሚዲያዎች እየተዘገበ መሆኑን የዝግጅት ክፍላችን አረጋግጦአል።

ፕሬዝዳንት ኦባማ ከአፍሪካ የጋበዙዋቸው የጋና ፣ የታንዛኒያና የቤኒን መሪዎች ያለምንም ተቃውሞ የሄዱበትን ተልእኮ ለማሳካት ሲችሉ በቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ጆርጅ ቡሽና የእንግሊዙ ቶኒ ብሌየር ጸረ ሽብር ዘመቻ አጋር ተደርጎ በየስብሰባው ሲጋበዝ የኖረው መለስ ዜናዊ ጋባዦቹን ጭምር ያሸማቀቀ ተቃውሞ እንደገጠመው በስፋት ከዘገቡት ትላልቅ የዜና ሚዲያዎች እንደ አጃንስ ፕሬስ፤ ዋሽንግተን ፖስት፤ ሃፊንግቶን ፖስት፤ ዩሮ ኒውስ፤ አቢሲ 2፤ ሄራልድ ሜል፤ ዘጋርዲያን፤ ጋዜቴ ኔት ወዘተ ሲሆኑ በኢትዮጵያ ወቅታዊ ጉዳይ ላይ የሚዘግቡ ሁሉም ድህረ ገጾች ዜናውን ተቀባብለውታል።

በአውሮፓ ውስጥ በተለይም በአውሮፓ ህብረት አባል አገሮች ከፍተኛ ተደማጭነት ያለው ዩሮ ኒውስ የተባለው የመገናኛ ተቋም ባወጣው ዘገባ፣ ከ400 በላይ የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን ምእራባዊያን መንግስታት አምባገነን መንግስታትን ለማስወገድ ከፍተኛ ትኩረት መስጠት ይገባቸው እንደነበር መናገራቸውን ገልጧል። ዩሮ ኒውስ የማርች ፎር ፍሪደም አስተባባሪ የሆኑትን ዶ/ር ካሳ አያሌውን ጠቅሶ እንደዘገበው "የተቃውሞው ዋና አላማ በምእራባዊያን እርዳታ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚሰፈነው አምባገነንነትና የጦር ወንጀል እንዲቆም ለመጠየቅ ነው።" የዩሮ ኒውሱ ዘጋቢ ስቴፋን ግሩቤ እንዳለው " አንዳንድ የአፍሪካ መሪዎች በጉባኤው ላይ እንዲካፈሉ መጋበዛቸው እና እነሱን ለመቃወም የወጡት የኢትዮጵያ ተቃዋሚዎች የሰጡት ድምቀት ፣ የአካባቢው ነዋሪዎች ትክክለኛ የቡድን 8 አገሮች ስብሰባ እየተካሄደ እንደሆነ እንዲሰማቸው አድርጓል" ብሎአል።

ዋሽንግተን ፖስት ባወጣው ዘገባ ደግሞ ኢትዮጵያውያን ያሰሙት ተቃውሞ በሜሪላንድ የሚኖሩ ዜጎችን ትኩረት በእጅጉ ስቧል። ዋሽንግተን ፖስት ሰልፈኞቹ "አሳፋሪ፣ ጨካኝ አምባገነን፣ ውሸታም፣ ጨፍጫፊ መሪ" የሚሉ መፈክሮችን እያሰሙ ሲያወግዙ እንደነበር ገልጧል።

ቼሪ ማገርስ የተባለች አሜሪካዊት በኢትዮጵያኑ የተቃውሞ ሰልፍ መገረሙዋን ገልጣ፣ በዚህ የታሪክ አጋጣሚ ውስጥ ለመሳተፍ መምጣቱን ተናግራለች።

አቢሲ 2 የተባለው የዜና ማሰራጫም በበኩሉ በ3 አውቶቡስ የተጫኑ ኢትዮጵያውያን የአገራቸውን ሰንደቅ አላማ እያውለበለቡ በባልቲሞር አካባቢ በመገኘት መለስ ዜናዊ የሚያደርሰውን የሰብአዊ መብት ጥሰት ተቃውመዋል። ሄራልድ ሜል የተባለው ድረገጽም እንዲሁ መለስ ዜናዊ በአለማችን ካሉ በሰብአዊ መብት ጥሰት ከሚታወቁት መካከል ግንባር ቀደሙ ነው ካለ በሁዋላ፣ በኦጋዴን የተፈጸመውን የሰብአዊ መብት ጥሰት አትቷል። ጋዜቴ ኔት የተባለው ድረገጽ በበኩሉ ተቃውሞው በኢትዮጵያ ውስጥ የሚፈጸመውን የጅምላ ግድያ ለአለም ለማሳወቅ መዘጋጀቱን ጠቁሟል።

የገዢው ፓርቲ ልሳናት እና የመንግስት የመገናኛ ብዙሀን አነስተኛ ሽፋን የሰጡት የዘንድሮው የቡድን ስምንት ጉባኤ ለዘረኛው ሥርዓት ቁንጮ መለስ ዜናዊና በውጭ ላሉ ደጋፊቹ ታላቅ ሽንፈት ፣ አገዛዙን ለሚቃወሙት ሀይሎች ግን ታላቅ ድል ተደርጎ ተቆጥሯል። በህወሃቱ ታጋይ ብርሃኔ ገብረክርስቶች ታኮነት የውጪ ጉዳይ ሚንስቴር ተደርጎ የተሾመው ሀይለማርያም ደሳለኝ ሹመቱን እንደተቀበለ፣ በውጭ የሚገኘው ኢትዮጵያዊ ከተቻለ ደጋፊ ካልተቻለ ተቃዋሚ እንዳይሆን የማድረግ ስትራቴጂ ለመከተል ወስኖ እየተንቀሳቀሰ መሆኑ ይታወቃል። ይሁን እንጅ በውጭ ያለው ኢትዮጵያዊ በዘረኛው መለስ አገዛዝ ላይ የሚሰማው ተቃውሞ እየጨመረ መሄዱ የአደባባይ ምስጥር ሆኖአል።

## ወያኔ በኦሞ ሸለቆ በሚኖሩ የሱሪ ና የቦዲ ብሄረሰብ አባላት ላይ እጅግ ዘግናኝ የሆኑ ግፎች እየፈጸመ መሆኑ ተዘገበ

የትላልቅ ወንዞቻችንን ተፋሰሶች ተከትለው የሰፈሩትን ዜጎች በማፈናቀል ለምና ድንግል የእርሻ ቦታዎችን ለውጪ ኩባንያዎች በርካሽ ዋጋ በመቸብቸብ መጠኑ የማይታወቅ ገንዘብ ለግላቸው እየሰበሰቡ ያሉ የወያኔ መሪዎች ከመሬታችን አንፈናቀልም በሚሉት ላይ የሚወስዱትን የሃይል እርምጃ በማጠናከር ላለፉት 3 ወራት አናሳ የህዝብ ቁጥር ያላቸውን የሱሪና የቦዲ ብሄረሰብ አባላትን እያጠቁ መሆኑን ለዝግጅት ክፍላችን የደረሰ ዜና አመለከተ።

የኦሞ ወንዝ ሸለቆ ውስጥ የሚኖሩትን ሁለቱን ብሄረሰቦች ከይዞታቸው በማፈናቀል መሬታቸውን የወሰደው አንድ የማሌዢያ ኩባንያ ሲሆን ኩባንያው ከህዝቡ ጋር ጠብ ውስጥ የገባው መሬት ከተፈጠረ ጀምሮ ተነክቶ የማይታወቀውንና ብርቅዬ የዱር አራዊቶች መኖሪያ የሆነውን ጥቅጥቅ ያለ ደን በትላልቅ ቡል ዶዘሮች መመንጠር እንደጀመረ መሆኑን ምንጮች ይናገራሉ።

በመለስ ዜናዊ ቀጥተኛ ትዕዛዝ የአካባቢው መሬት ተሰጥቶታል የሚባለው የማሌዢያው ካምፓኒ ለአገዳ ልማት የአካባቢው ህዝብ የህልውና መሰረት የሆነው የቆቃ ወንዝ አቅጣጫው በመቀየር የወንዙ መደራሻ የነበሩ ቦታዎች ሁሉ ውሀ አልባ እንዲሆኑ በማድረግ በአካባቢው ተፈጥሮ ላይ ትልቅ ጉዳት እንዳደረሰ ይነገራል።

በዚህም የተነሳ ሱሪዎች ተቃውሞአቸውን ለመግለጽ ኩባንያው እርሻ ላይ ከብቶቻቸውን በመልቀቃቸው የኩባንያው ባለስልጣናት ችግሩን ለወረዳው ባለስልጣናት እንደገለጹና የወረዳው ባለስልጣናትም ሱሪዎችን ከመከላከያ ሰራዊት በስተቀር የሚያቆማቸው የለም በማለት መከላከያ ሰራዊት ወደ አካባቢው እንዲሰማራ በመጠየቅ ማጂ እየተባለ በሚጠራው የገበያ ሥፍራ ላይ የወያኔ ጦር በከፈተው ተኩስ 65 የብሄረሰቡ አባላት በአንድ ቀን ሲገደሉ ከቀናት ቦኋላ ደግሞ ሌሎች 5 ሰዎች በተጨማሪ ህይወታቸውን እንዲያጠ መደረጉን ለማወቅ ተችሎአል።

ወያኔ ዜጎቹን ለማፈናቀል የተጠቀመበት የሰፈራ ፕሮግራም የሚባለውን በ ዕቅድ ላይ ያልተዘጋጀ መንደር ሁሉም የብሄረሰቡ አባላት ስላልተቀበሉት በጠመንጃ እያስገደዱ ለማስፈር ጥረት ቢደረግም በህዝቡ እንቢተኛነት ሙከራው ስላልተሳካ የጅምላ እስርና ግርፋት ተጀምሮአል የሚሉ ምንጮች ከመሬታችን አንፈናቀልም በማለታቸው ብቻ በርካታ ሱሪዎች እጃና እግራቸውን የፊጥኝ እየታሰረ ለቀናት አውላላ ሜዳ ላይ እንዲቆዩ በመደረጉ ብዙዎች እግሮቻቸውና እጆቻቸው ከጥቅም ውጭ እንዲሆን መደረጉን ይመሰክራሉ። በእስር ላይ እያሉ የተገደሉ፤ በአካባቢው የተሰማሩት የፌደራል ፖሊስ እና ወታደሮች፣ የተጸዳዱባቸውን ሽንት ቤቶች እያነሱ እጃቸውና እግራቸው የፊጥኝ በታሰሩት ሱሪዎች አናት ላይ በመድፋት የሚያሰቃዩዋቸው ሰዎች ቁጥር ቀላል እንዳልሆነ ይነገራል።

በሱሪዎች ላይ የሚፈጸመው ግፍ በዚህ ብቻ አያበቃም። ፖሊሶች ከሱሪዎች ጋር በግጦሽ መሬት የተነሳ የሚፋለሙትን ዲዚዎች ወደ እስር ቤት በማስገባት ሱሪዎችን እንዲደበድቡና ማንነታቸውን እንዲያዋርዱ ያደርጋሉ። (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz
አ<u>ጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org